# ገንዘብ ሚኒስቴር

## የታክስ ከፋዩን ሀብት ስለመያዝና ስለመሸጥ

## የወጣ መመሪያ ቁጥር 6/2011

ገንዘብ ሚኒስቴር
መጋቢት 2011 ዓ.ም

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
Ministry of Finance ARCHIVES

# የታክስ ከፋዮችን ሀብት ስለመያዝና ስለመሸጥ የወጣ
## መመሪያ ቁጥር 6/2011

1. <u>አውጪው ባለሥልጣን</u>

የገንዘብ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር አንቀጽ 136 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## አጠቃላይ ድንጋጌዎች

2. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "**የታክስ ከፋዮችን ሀብት ስለመያዝና ስለመሸጥ የወጣ መመሪያ ቁጥር 6/2011**" <u>ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፤</u>

3. <u>ትርጓሜ</u>

በታክስ አስተዳደር አዋጁ ትርጉም የተሰጠው ቃል ወይም ሀረግ በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ በፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጁ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም፡-

ሀ) **"ሀብት"** ማለት የመያዣ ትዕዛዝ ሊወጣባቸው ከማይችሉት ሀብቶች በስተቀር ታክስ ከፋዩ በሊዝ የያዘውን መሬት ጨምሮ ማናቸውም ቤት ወይም ህንጻ፣ የንግድ ሥራ የሚከናወንበት ድርጅት፣ ልዩ ልዩ እቃዎች፣ በሌላ ሰው ዘንድ ያለው ወይም በሌላ ሰው ዘንድ የሚገኝ ወይም የሚከፈለው ገንዘብ፣ ቼኮች፣ የሚተላለፉ ሰነዶች፣ቦንዶች ወይም ለገንዘብ የተሰጡ ሌሎች ዋስትናዎች፣ በኩባንያ ውስጥ ያለው የአክሲዮን ድርሻ፣ በጋራ በተያዙ ሀብቶች ላይ ያለው ድርሻ ወይም ማናቸውም ሊሸጡ የሚችሉ ሌሎች ሀብቶች ናቸው፡፡

ለ) **"ሀብት ማስከበር"** ማለት የታክሱ ባለስልጣን የታክስ ከፋዩን ሀብት ወይም ንብረት ከመያዙ በፊት ባለበት እንዲቆይና እንዳይንቀሳቀስ የሚወስደው እርምጃ ነው፡፡

ሐ) "ታክስ" በገቢ ዕቃዎች ላይ የተጣለን ቀረጥና ታክስ እና አስተዳደራዊ ቅጣትን ይጨምራል፡፡

መ) **"መያዝ"** ማለት በማናቸውም መንገድ የታክስ ከፋዩን ሀብት መያዝ እንዲሁም የታክስ ከፋዩ የሆነ ገንዘብ/ሀብት በእጁ ከሚገኝ ሰው ታክስ መሰብሰብን ይጨምራል፡፡

ሠ) **"የታክስ ባለሥልጣን"** ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ወይም የአዲስ አበባ ከተማ እና የድሬደዋ አስተዳደር ገቢዎች ባለስልጣን ነው።

ረ) **"አዋጅ"** ማለት የፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ነው፡፡

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአዋጁ አንቀጽ 41 መሰረት በታክስ መክፈያ ጊዜው ታክሱን ባልከፈለ ታክስ ከፋይ እንዲሁም በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 በአንቀፅ 119(5)፡122(6) እና 148(2) እንደቅደም ተከተላቸው፣ በገቡት የዋስትና ግዴታ መሠረት ባልተወጡ፣ በልዩነት ቀረጥና ታክስ በሚፈለግባቸው እና አስተዳደራዊ ቅጣት በተጣለባቸው ላይ ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. ለታክስ አሰባሰቡ ተግባር ሀብት የሚያዝበት መንገድ

1. የታክስ ግዴታቸውን ያልተወጡ ሰዎች የሚፈለግባቸው ታክስ በሚከተለው አኳኋን ሊሰበሰብ ይችላል፡፡

   ሀ) የታክስ ባለእዳውን የሚንቀሳቀስ ሀብት በመያዝ እና በመሸጥ፣

   ለ) የታክስ ባለእዳውን የማይንቀሳቀስ ወይም ልዩ ተንቀሳቃሽ ሀብት በማስከበር፣ በመያዝ እና በመሸጥ፣

   ሐ) የታክስ ግዴታውን ያልተወጣ ሰው ሀብት በእጁ የሚገኝ ወይም ለታክስ ከፋዩ ማናቸውም ግዴታ ያለበት ሰው የያዘውን ሀብት ለባለስልጣኑ እንዲያስረክብ ወይም በአዋጁ የተጣለበትን ግዴታ እንዲወጣ በማድረግ፡፡

2. የታክስ ባለእዳውን የንግድ ሥራ ሀብት ጨምሮ ማናቸውም የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ሀብት እስኪሸጥ ድረስ የማስተዳደር ተግባር የሚከናወነው ባለስልጣኑ በሚመድባቸው ተረካቢዎች ይሆናል፡፡

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
Ministry of Finance ARCHIVES 2

## 5. <u>የታክስ ባለስልጣኑ ስልጣንና ተግባር</u>

የታክስ ባለስልጣን፡-

1) በታክስ እዳ ምክንያት ሀብት ለመያዝ፣ ለማስከበርና የግልጽ ጨረታ ሽያጭ ለማካሄድ ማስታወቂያዎችን ያወጣል፣

2) ሀብት ለመያዝ፣ለማስከበር፣ የንግድ ድርጅት ለማሸግ ተግባር አፈጻጸም ድጋፍ የሚሰጡ የፖሊስ አካላትና የአካባቢው የቀበሌ አስተዳደር ተወካዮች እንዲገኙ ያደርጋል፡፡

3) ለታክስ እዳ የተያዘ ወይም እንዲከበር የተደረገ ተንቀሳቃሽ ሀብት ለሀብቱ ማቆያ ወይም ማከማቻ ወደ ተዘጋጀ ቦታ እንዲጓጓዝ ያደርጋል፡፡ የንግድ ሥራ የሚካሄድበትን ጨምሮ ማናቸውም የታክስ ከፋይ የማይንቀሳቀስ ሀብት ባለበት ተከብሮ እንዲቆይ ወይም እንዲታሸግና ጥበቃ እንዲደረግለት ያደርጋል፡፡

4) በታክስ እዳ ምክንያት ለሚያዝ ሀብት ማቆያ/ማከማቻ/ የሚውል ቦታ ተገቢውን የጥበቃ አገልግሎት ከመንግስታዊ እና ሌሎች አካላት ማግኘቱን ይከታተላል፡፡

5) በታክስ እዳ ምክንያት የተያዘ ሀብትን ግምት የሚያከናውኑ አካላት የግምቱን ሥራ በወቅቱ ስለማከናወናቸው ይከታተላል፡፡

6) በታክስ እዳ ምክንያት የተያዘን ወይም የተከበረን ሀብት የግልጽ ጨረታ መነሻ ዋጋ ግምት የሚያከናውኑ አካላት የግምቱን ሥራ በወቅቱና በአግባቡ ማከናወናቸውን ይከታተላል፡፡

7) በግልጽ ጨረታ ለመሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች በጨረታ የሚሸጠውን ሀብት በቦታው ተገኝተው ማየት እንዲችሉ ሀብቱ የሚገኝበት ቦታ በሥራ ሰዓት ለተመልካቾች ክፍት እንዲሆን ያደርጋል፡፡

8) በታክስ እዳ ምክንያት የተያዘን ሀብት ለመሸጥ የሚሠራጨውን የግልጽ ጨረታ ሽያጭ ሰነድ ያጸድቃል፡፡

9) በታክስ ዕዳ ምክንያት የተያዘ ሀብት በአንድ ጊዜ ወይም በቅደም ተከተል በግልጽ ጨረታ እንዲሸጥ ያደርጋል፡፡

10) በታክስ እዳ ምክንያት የተያዘ ሀብት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በግልጽ ጨረታ አማክሎ የሚሸጥበትን ዘዴ ሊወስን ይችላል፡፡

11) የተያዘው/የተከበረው ሀብት የሚተላለፍ የገንዘብ ሠነድ ወይም በኩባንያው ውስጥ ያለ ድርሻ ወይም በውርስ የተገኘ ሀብት የሆነ እንደሆነ ሽያጩን ለማካሄድ ሦስተኛ ወገን ለመጠቀም ይችላል፡፡

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
Ministry of Finance ARCHIVES 2

12) በግልጽ ጨረታ የተሸጠ ሀብት ዋጋ ሙሉ በሙሉ መከፈሉን በማረጋገጥ የሀብቱ ባለቤትነት በገኘው ስም እንዲዛወር ለሚመለከተው የመንግስት አካል ያስታውቃል፡፡

13) በዚህ መመሪያ መሠረት ከሁለተኛ ጊዜ ግልጽ ጨረታ በኋላ ያልተሸጠን ሀብት በመነሻ ግምቱ ዋጋ ይረከባል፡፡

14) የታክስ ባለስልጣን ሠራተኞች ወይም ከእነርሱ ጋር ዝምድና ወይም ግንኙነት ያላቸው ሰዎች የታክስ ባለእዳውን ሀብት ለመግዛት በግልጽ ጨረታ እንዳይሳተፉ ይደረጋል፡፡

15) በታክስ እዳ ምክንያት ከሀብት መያዝ፣ ማስከበርና መሸጥ ጋር የተያያዙ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል፡፡

## 6. የታክስ ባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር

የታክስ ባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ፣

1) የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ደርሷቸው የሚፈለግባቸውን ታክስ ላልከፈሉ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው አባሪ መሠረት የክፍያ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

2) ታክስ ከፋዩ የታክስ አሰባሰቡን የሚያደናቅፍ ሀብት የማሸሸ ወይም ሌላ ተመሳሳይ ተግባር በመፈጸም ላይ ያለ መሆኑን ሲረዳ የታክስ እዳ ክፍያ ማስታወቂያ ከተላከ በኋላ መቆየት ያለበትን የ30 ቀናት ጊዜ ገደብ ሳይጠብቅ በአፋጣኝ ሀብቱን የመያዝ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

3) የሚያዘው ሀብት የሚበላሹ ዕቃዎች በሚሆኑበት ጊዜ የታክስ እዳ ክፍያ ማስታወቂያ ከተላከ በኋላ መቆየት ያለበትን የ30 ቀናት ጊዜ ገደብ ሳይጠብቅ ዕቃዎቹ የሚሸጡበትን ጊዜና የሚሸጡበትን ስርዓት ይወስናል፡፡

4) ሀብት ስለመያዝ የሚሰጥ ማስታወቂያ የደረሰው ወይም ሀብቱ የተያዘበት ታክስ ከፋይ የታክስ እዳውን የመክፈያ ጊዜ እንዲራዘምለት ወይም ታክስ ከፋዩ በየጊዜው በሚደረግ ክፍያ የሚፈለግበትን ታክስ ለመፈጸም እንዲፈቀድለት በሚያቀርበው ጥያቄ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

5) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የታክስ ባለዕዳውን ሀብት የመያዝና የመሸጥ አፈጻጸም እንዲቆም ያደርጋል፡፡

6) በታክስ እዳ የተያዘን የታክስ ከፋዮች ሀብት የመያዝና የመሸጥ ተግባር በሌሎች አካላት እንዲከናወን ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በዚህ ረገድ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል፡፡



Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2

## ክፍል ሁለት
## የታክስ ባለእዳን ሀብት ስለመያዝ

7. ሀብትን ስለመያዝ የሚሰጥ ማስታወቂያ፡-

ሀብትን ስለመያዝ የሚሰጥ ማስታወቂያ የሀብት መያዝ እርምጃ ከመወሰዱ ከ30 ቀናት አስቀድሞ ለታክስ ከፋዩ መሰጠት ወይም መድረስ ያለበት ሲሆን ማስታወቂያውም ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው አባሪ 2 የተዘረዘሩትን የሚከተሉን መረጃዎች የያዘ መሆን አለበት፡፡

1) ከታክስ ባለስልጣኑ ቀደም ሲል ለታክስ ከፋዩ የተላከውን የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ቀን

2) ከታክስ ከፋዩ የሚፈለገውን የታክስ እዳ የገንዘብ መጠን
   - ✓ የሚጠበቅበትን የታክስ እዳ
   - ✓ ማስታወቂያው እስከተላከበት ጊዜ ድረስ የታሰበው ወለድ
   - ✓ መቀጫዎች
   - ✓ አስቀድሞ የተከፈለ የታክስ እዳ ካለ ተቀናሽ የተደረገ መሆኑን፣ እና
   - ✓ በቀሪነት የሚፈለግበትን ታክስ

3) ባለስልጣኑ የታክስ ከፋዩን ሀብት በመሸጥ ከሽያጭ የሚገኘውን ገንዘብ የታክስ እዳውን ብቻ ሳይሆን ሀብቱን ከመሸጥ ጋር በቀጥታ ለተያያዙ የአፈጻጸም ተግባሮች ማከናወኛ ለሚወጣ ወጪ መሸፈኛ የሚያውለው መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ መጻፍ ይኖርበታል፡፡

8. <u>ሀብትን ስለመያዝ ማስታወቂያ ስለሚሰጥበት ሁኔታ</u>

1) ሀብትን ስለመያዝ የሚሰጠው ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ በሚከተለው አኳኋን እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

   ሀ) ታክስ ከፋዩ ነዋሪነቱ በኢትዮጵያ በማይሆንበት ጊዜ:--
   1. ድርጅት ከሆነ በድርጅቱ የንግድ ሥራ ቦታ ለሚገኘው የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም ለታክስ እንደራሴው ወይም ለታክስ ወኪሉ በአካል በመስጠት፣
   2. ግለሰብ ከሆነ በቀጥታ ለታክስ ከፋዩ፣ ወይም ለታክስ እንደራሴው ወይም ለታክስ ወኪሉ በአካል በመስጠት፡፡

   ለ) ታክስ ከፋዩ በኢትዮጵያ ነዋሪ ካልሆነ፡-

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
Ministry of Finance ARCHIVES 2

1. በኢትዮጵያ ወኪል የሆነው ድርጅት የንግድ ሥራ ቦታ ለሚገኘው የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም እንደራሴ ወይም ወኪል በአካል በመስጠት

2. ግለሰብ ከሆነ ለታክስ እንደራሴው ወይም ወኪሉ በአካል በመስጠት፡፡

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ቁጥር ሀ እና ለ መሰረት ማስታወቂያውን የሚቀበለው ወይም የሚረከበው ሰው በማስታወቂያው ቅጅ ላይ የተቀበለ ለመሆኑ ማረጋገጫ እንዲሆን ስሙንና የተረከበበትን ቀን በመጻፍ ሊፈርም ይገባል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ለታክስ ከፋዩ ማስታወቂያውን መስጠት ካልተቻለ በታክስ ከፋዩ ወይም በወኪሉ የሙያ ወይም የንግድ ሥራ ማከናወኛ ቦታ ወይም መኖሪያ ቤት አመችና በግልጽ በሚታይ ስፍራ ሶስት እማኞችን በማስፈረም ወይም የፖሊስ መኮንን በተገኘበት እንዲለጠፍ ይደረጋል፡፡

3) በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት ለታክስ ከፋዩ የታክስ ማስታወቂያ ውሳኔውን ማድረስ ካልተቻለ ነዋሪነቱ በኢትዮጵያ የሆነ ግለሰብ ወይም ድርጅት ከሆነ ታክስ ከፋዩ በተመዘገበበት የድርጅቱ ወይም የግለሰቡ አድራሻ በሪኮማንዴ ደብዳቤ በመላክ፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1፣ 2 እና 3 መሰረት ማስታወቂያዎችን ለታክስ ከፋዩ ማድረስ ካልተቻለ እንደ አስፈላጊነቱ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ኢሜልና ፋክስን ጨምሮ ለታክስ ከፋዩ በማስተላለፍ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

5) በዚህ አንቀጽ የተመለከቱትን ዘዴዎች በመጠቀም ማስታወቂያ ማድረስ ካልተቻለ የፍርድ ቤት ማስታወቂያዎች በሚወጡበት ጋዜጣ ማስታወቂያውን በማውጣት ለታክስ ከፋይ እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት የፍርድ ቤት ማታወቂየዎች በሚወጡበት ጋዜጣ የሀብት መያዣ ትዕዛዝ የወጣበት ታክስ ከፋይ የታክስ ማስታወቂያ ውሳኔ እንደደረሰው ይቆጠራል፡፡

## 9. <u>ሀብት ከመያዙ በፊት ስለሚወሰዱ እርምጃዎች</u>

1) የታክስ ባለስልጣኑ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ከደረሰበት ወይም በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ውሳኔ ከተሰጠበት ወይም ይግባኝ ቀርቦ በታክስ ይግባኝ ጉባኤ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ወይም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 መሠረት ማስጠንቀቂያ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ የታክስ ባለእዳውን ሀብትና የሥራ



Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
Ministry of Finance ARCHIVES 2

እንቅስቃሴ የሚመለከት መረጃ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በመሆን ማሰባሰብ አለበት።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚሰበሰበው መረጃ የታክስ ባለእዳውን ሀብት ዓይነት፣ ብዛት፣ የሚገኝበትን አድራሻ፣ የታክስ ከፋዩ ሀብት በማን ይዞታ ሥር እንደሚገኝ፣ በዋስትና የተመዘገበ መሆን አለመሆኑን የመሳሰሉ መረጃዎችን የሚጨምር መሆን አለበት።

3) በተሰበሰበው መረጃ ወይም በተገኘ ጥቆማ መሰረት የሚመለከተው የታክስ ባለስልጣን የበላይ ኃላፊ የታክሱን አሰባሰብ የሚያደናቅፍ ሁኔታ መኖሩን የተረዳ እንደሆነ እና ታክስ ከፋዩ ለመክፈል ፈቃደኛ አለመሆኑ ከታወቀ የ30 ቀናት የጊዜ ገደብ ወይም በማስጠንቀቂያ የተሰጠውን ቀነ ገደብ ሳይጠብቅ ባለሥልጣኑ ሀብቱን በመያዝ ታክስ የመሰብሰቡ አፈጻጸም እንዲካሄድ ትዕዛዝ ይሰጣል።

4) ሀብቱን የመያዝ ትዕዛዝ ለታክስ ባለእዳው፣ ለታክስ ባለእዳው እንደራሴ ወይም ለታክስ ባለእዳው ወኪል፣ የታክስ ባለእዳው ሀብት በእጁ ወይም በይዞታው ለሚገኝ ለማንኛውም ሰው፣ ሀብቱን ወይም መብቱን ወይም ምርጫውን ለሚመዘግብ አግባብ ላለው ሰው ወይም ፍርድ ለሚያስፈጽም አካል መሰጠት አለበት።

## 10. <u>ሀብትን ስለማስከበር</u>

1) የታክስ ባለስልጣኑ ለታክስ ከፋዩ ማስጠንቀቂያውን ለመላክ ሲወስን ወዲያውኑ የታክስ ከፋዩ ሀብት በዋስትናነት እንደተሰጠ ሀብት ሳይሸጥ፣ ሳይለወጥ፣ ሳይከፈል፣ በባለሀብትነትም ሆነ በይዞታ ሳይዛወር ተከብሮ እንዲቆይ እንዲያደርግ ለታክስ ከፋዩ፣ ሀብት ለሚመዘግብ አግባብ ያለው የመንግስት አካል ወይም የግል ድርጅት ወይም የታክስ ከፋዩ ሀብት በእጁ ለሚገኝ ሰው ማስታወቂያ ይልካል።

2) ሀብት ተከብሮ እንዲቆይ የሚሰጥ የማስታወቂያ ይዘት ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው አባሪ 3 የተዘረዘሩትን መረጃዎች የያዘ መሆን አለበት።

3) ሀብት የሚመዘግበው አካል በታክስ ከፋዩ ስም የተመዘገበ ሀብት ተከብሮ እንዲቆይ ማድረግና የተከበረውን ሀብት ዓይነት ለታክሱ ባለስልጣን ማስታወቅ አለበት።

4) የታክስ ከፋዩ ሀብት በእጁ የሚገኝ ማናቸውም ሰው ሀብት የማስከበሩ ማስታወቂያ ባይደርሰው ኖሮ ሀብቱን ለታክስ ከፋዩ የሚያስረክብ መሆኑን እና ሀብቱ በእጁ ወይም በይዞታው እንዲቆይ መደረጉ ወጪ ያስከተለበት መሆኑን በበቂ ማስረጃ አስደግፎ ያቀረበ እንደሆነ የዚህ ዓይነቱ ወጪ ተሰልቶ ከሀብቱ ሽያጭ ከተገኘ ገቢ ላይ እንዲከፈለው ይደረጋል።

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
Ministry of ... ARCHIVES 2 ... nance

## 11. ስለማይከበሩና ስለማይያዙ ሀብቶች

1. ከዚህ በታች የተመለከቱት ሀብቶች በታክስ እዳ ምክንያት የማይከበሩና የማይያዙ ናቸው፡

   ሀ) ለታክስ ባለእዳውና ለቤተሰቡ የእለት አገልግሎት የሚያስፈልጉ ልብሶች፣ ለምግብ ማብሰያ አገልግሎት የሚውሉ ቁሳቁሶች፣ አልጋ፣ የአልጋ ልብስ፣ ፍራሽ ፣ ትራስ እና ብርድ ልብስ፣

   ለ) ለሙያ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ የእጅ መሳሪያዎች፣

   ሐ) የታክስ ባለእዳው በግብርና ስራ የሚተዳደር ከሆነ በባለስልጣኑ አስተያየት ለስራው አገልግሎት በቂ ሆነው የሚገመቱ የቀንድ ከብቶች፣ የጋማ ከብቶች፣ የዘር እህልና ፍጹም አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች፣

   መ) ለታክስ ባለእዳውና ለቤተሰቡ ለ3 ወራት መተዳደሪያ የሚሆን ገንዘብ ወይም ቀለብ፣

   ሠ) የታክስ ባለእዳው የሚያገኘው የጡረታ ገንዘብ፣ ባል/ሚስት ለሚስቱ/ለባልዋ ከፍቺ በኋላ ለልጆች ቀለብ የሚከፍሉት ገንዘብ፣

   ረ) በሠንጠረዥ "ሀ" ከታክስ ነጻ ከተደረገው የገቢ መጠን ሳያልፍ ሠራተኛው የሚያገኘው ደመወዝ ወይም ማናቸውም በተወሰነ ጊዜ የሚገኝ ሌላ ገቢ፣

   ሰ) የባልና ሚስት የቃል ኪዳን ቀለበት፣ሜዳሊያ/ኒሻን፣

   ሸ) የጠበቆቹ፣ የሀኪሞች እና የአካውንታንቶች/ኦዲተሮች ፋይሎችና ሠነዶች፣ ነገር ግን የግል ወይም የሙያ ጉዳዮችን ፋይሎች የያዘ ኮምፒተር በተያዘ ጊዜ መከተል ስለሚገባው የአፈጻጸም ሥርዓት ባለስልጣኑ ውሳኔ ይሰጣል፣

   ቀ) እንዳይከበር፣ እንዳይሸጥና ለእዳ መክፈያ እንዳይሆን በማናቸውም ሌላ ሕግ ወይም በፍርድ ቤት የተወሰነ ማናቸውም ዓይነት ሀብት፣

2. መያዝ፣ መሸጥና ማዘዋወር በሕግ ክልከላ የተደረገባቸው እቃዎች፣ ለመያዝ፣ ለመጠቀም ወይም ለመሸጥ ልዩ ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው እቃዎች፣ በሕግ መሠረት የሚወረሱ ወይም ኮንትሮባንድ፣ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው እቃዎች ከተገኙ አግባብ ያለውን አካል በማሳወቅ እንዲረከቡ ማድረግ ወይም አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ መደረግ አለበት፣

3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1፣(ለ)(ሐ) እና (መ) አፈጻጸም ባለስልጣኑ የማይከበር ሀብትን መጠን ሊወስን ይችላል።

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
Ministry of ... ARCHIVES ... Finance

## 12. ሀብት ስለመያዝ

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 መሠረት ማስጠንቀቂያ የተሰጠው ታክስ ከፋይ ማስጠንቀቂያው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ የታክስ እዳውን ያልከፈለ እንደሆነ ወይም በታክስ ባለስልጣኑ ቀርቦ የመክፈያ ጊዜ እንዲሰጠው ያላደረገ ወይም በቂ ዋስትና ያላቀረበ እንደሆነ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 11 ከመያዝ ነጻ ከተደረጉት ወይም በፍ/ቤት አስቀድሞ ከተከበረ ወይም በዋስትና ከተያዘ ሀብት በስተቀር ማናቸውንም የታክስ ባለእዳውን ሀብት ባለስልጣኑ ይይዛል፣ ለታክስ እዳው ክፍያ እንዲውል ያደረጋል።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ባለስልጣኑ ታክስ ከፋዩ የታክስ አሰባሰቡን የሚያደናቅፍ፣ ሀብት የማሸሽ ወይም ሌላ ተመሳሳይ ተግባር በመፈጸም ላይ ያለ መሆኑን ሲረዳ የታክስ እዳ ክፍያ ማስታወቂያ ከተላከ በኋላ መቆየት ያለበትን የ30 ቀናት ጊዜ ገደብ ሳይጠብቅ በአፋጣኝ ሀብቱን የመያዝ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል።

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የሚያዘው ሀብት በተቻለ መጠን ከታክስ ባለእዳው ከሚፈለገው የታክስ እዳ ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት።

4) የታክስ ባለስልጣኑ ሀብት ከመያዙ በፊት ሀብቱ እንዲያዝ የተሰጠውን የውሳኔ/የትዕዛዝ ቅጅ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ለተገለጹት አካላት መስጠት አለበት።

5) ከእርሻ ሰብል በስተቀር

   ሀ) ማናቸውም የሚንቀሳቀስ ሀብት የሚያዘው በታክስ ባለእዳው እጅ የሚገኘውን ሀብት በመረከብ ነው።

   ለ) የታክስ ባለእዳው ወይም ወኪሉ በተገኙበት የታክሱ ባለሥልጣን ሀብቱን ቆጥሮና መዝግቦ ይረከባል፣ በቦታው የተገኙት ሁሉ የተቆጠረውን ሀብት በፊርማቸው ያረጋግጣሉ፣ የተቆጠረው ሀብት ዝርዝር ቅጅ ለታክስ ባለእዳው ይሰጣል።

   ሐ) የተያዘው ሀብት የከበሩ ማእድናት ማለትም አልማዝ፣ እንቁ፣ ወርቅና ብር የሆነ እንደሆነ መጠኑ በሚዛን ተመዝኖ እና የጥራት ደረጃው ተመርምሮ ዋጋው በባለሙያ ተገምቶ በዝርዝሩ ላይ መገለጽ አለበት።

6) የተያዘው ወይም የተከበረው ሀብት በቀላሉ የሚበላሽ ወይም ዋጋ የሚያጣ/የሚቀንስ የሆነ እንደሆነ ባለስልጣኑ በማናቸውም ዘዴ ወዲያውኑ ሊሸጠው ይችላል።

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
የመዝገብና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2
Ministry of Finance
ARCHIVES
2

7) የሚያዘው ወይም የሚከበረው ሀብት የእርሻ ሰብል ወይም ፍራፍሬ የሆነ እና በማሳው ላይ ያለ ከሆነ ትዕዛዙን በሥፍራው በመለጠፍ፣ ሰብሉ ታጭዶ የተከመረ ወይም በመወቃት ላይ ያለ ወይም የእንስሳት መኖ ክምር ከሆነ በክምሩ ወይም በአውድማው አቅራቢያ በመለጠፍ ይሆናል፡፡

8) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 የተከበረው ሀብት ስለሚጠበቅበት ሁኔታ የታክስ ባለስልጣኑ የሚሰጠው ትዕዛዝ እንደተጠበቀ ሆኖ የታክስ ባለእዳው ሰብሉን የባለስልጣኑ ተወካይ ባለበት ሊያጭድ ወይም ሊወቃ ይችላል፡፡

9) ለዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 7 አፈጻጸም የታክስ ባለእዳው ሰብሉን ካጨደ ወይም ከወቃ በኋላ የተገኘውን የምርት መጠን የባለስልጣኑ ወኪል ባለበት ተቆጥሮ ሁሉም እንዲፈራረሙ ከተደረገ በኃላ ሃብቱ የሚጠበቅበትንና የሚሸጥበትን ሁኔታ ባለስልጣኑ ይወስናል ፡፡

10) እንዲያዝ ወይም እንዲከበር የታዘዘው ሀብት በታክስ ባለእዳው እጅ ያልገባ ከሌላ ሰው የሚጠይቀው በሚተላለፍ ሰነድ ያልተደገፈ ገንዘብ ወይም በፍርድ ቤት ክስ በማስፈረድ መብት ያገኘበት ገንዘብ ወይም ሌላ ሀብት በሆነ ጊዜ የታክስ ባለስልጣኑ ሌላ ግልጽ የሆነ ትዕዛዝ እስኪሰጥ ድረስ ሀብቱ ወይም ገንዘቡ በእጁ ያለ ሰው ገንዘቡን ወይም ሀብቱን ለታክስ ባለእዳውም ሆነ ለሌላ ማናቸውም ሰው ሳይሰጥ /ሳያስተላልፍ በእጁ እንዲያቆይ በጽሁፍ ማዘዝ ይኖርበታል፡፡

11) የሚያዘው ወይም የሚከበረው ሀብት የታክስ ባለእዳው ከሌሎች ሰዎች ጋር በተካፋይነት ወይም በጋራ የሚጠቀምበት ወይም የጋራ ባለሀብት የሆነበት ሀብት ወይም በሽርክና የያዘው ሀብት ወይም በውርስ የተገኘ ሀብት ሲሆን የመያዙ ወይም የማስከበሩ ሥርዓት የሚፈጸመው ድርሻውን ለሌላ ሰው አሳልፎ እንዳይሰጥ፣ እንዳይሸጥ፣ በዋስትና እንዳያሲዝ ወይም በማናቸውም ምክንያት እንዳያስተላልፍ ከሽርክናው የሚያገኘውን ትርፍ እንዳይወስድ የማገድ ትዕዛዝ ለጋራ ባለሀብቶቹ ወይም ለሸሪኮች በመስጠት ነው፡፡

12) የሚያዘው ሀብት የታክስ ባለእዳው የሚያገኘው ደመወዝ በሚሆንበት ጊዜ በየወሩ እየተቀነሰ ወይም የታክስ ባለስልጣኑ በሚያዘው ሁኔታ እንዲያዝ ይደረጋል፡፡ የማንኛውም ሠራተኛ ደመወዝ እንዲያዝ የሚሰጠው ትዕዛዝ ከሠራተኛው የሚፈለገውን የታክስ እዳ መጠን እና የሚያዘውን የገንዘብ መጠን የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

13) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 12 ድንጋጌ መሠረት ተቀናሽ የሚደረገው መጠን በአዋጁ አንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ለሠራተኛው ከሚከፈለው ደመወዝ የሥራ ግብር ተቀናሽ ሆኖ ከሚደርሰው አንድ-ሶስተኛ መብለጥ የለበትም፡፡

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቤት ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
Ministry of Finance ARCHIVES 2

14) እንዲያዝ የታዘዘው ሀብት የሚተላለፍ የገንዘብ ሰነድ የሆነ እንደሆነ እና በፍርድ ቤት ወይም በመንግስት መስሪያ ቤት ያልተያዘ ከሆነ የማስከበሩ ወይም የማስያዙ ሥርዓት የሚፈጸመው የሚተላለፈው የገንዘብ ሰነድ ተይዞ በታክስ ባለስልጣኑ እንዲቀመጥ በማድረግ ወይም በሌላ አካል የተያዘም ከሆነ ሌላ ትእዛዝ እስከሚሰጥ ድረስ እንዳይለቀቅ የሚያግድ ትእዛዝ በመስጠት ይሆናል

15) እንዲያዝ ወይም እንዲከበር የታዘዘው ሀብት በፍርድ አስፈጻሚ መ/ቤት ወይም በመንግስት መስሪያ ቤት እጅ የሚገኝ ከሆነ ሀብቱ ወይም ሀብቱ የሚያስገኘው ማናቸውም ጥቅም ተጠብቆ እንዲቆይ የታክስ ባለስልጣኑ ትዕዛዝ በመስጠት ማስከበር ይችላል።

16) የታክስ ባለእዳው በውድ እቃዎች ማስቀመጫ ሳጥን ውስጥ ስላለው ሀብት መረጃ እንዲሰጥ ተጠይቆ ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም ቁልፉን ለመስጠት እምቢተኛ ከሆነ ባንኩ ወይም የገንዘብ ተቋሙ ቁልፉን እንዲሰጥ በማድረግ የባንኩ ተወካይና የታክስ ባለእዳው ወይም ወኪሉ እንዲገኙ ማስታወቂያ በመስጠት በታክስ ባለስልጣኑ ተከፍቶ ሀብቱ እንዲመዘገብና እንዲታሸግ ይደረጋል።

17) የመንግስት ቦንድ ወይም ከኢንቨስትመንት ወይም ከኢንሹራንስ በየጊዜው የሚከፈል ሂሳብ እንዳይከፈልና ሌላ ትዕዛዝ በታክስ ባለስልጣኑ እስከሚሰጥ ድረስ ተይዞ እንዲቆይ ለሚመለከተው አካል ትዕዛዝ በመስጠት ሊከበር ይችላል።

18) እንዲያዝ ወይም እንዲከበር የተወሰነው የማይንቀሳቀስ ወይም ልዩ ተንቀሳቃሽ ሀብት ከሆነ የታክስ ባለእዳው ሀብቱን ለሌላ ሰው እንዳይሰጥ፣ እንዳይሸጥ፣ እንዳይለውጥ ወይም በማናቸውም ሌላ ሁኔታ መብቱን ለማንም ሰው እንዳያዛውር እንዲሁም ሌሎች ሰዎች በሀብቱ ላይ የዋስትና መብትን ጨምሮ ማንኛውንም ዓይነት መብት እንዳይኖራቸው የሚያግድ ትዕዛዝ የማይንቀሳቀስ ሀብት ለሚመዘግበው አካል በመስጠት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

## 13. <u>የደንበኞችን ሀብት ስለመመለስ</u>

የተያዘው ወይም በማሸግ የተከበረው ሀብት የድርጅቱ ደንበኞች ሀብት በውስጡ የሚገኝበት እንደ ላውንደሪ/የደረቅ እጥበት፣ልብስ ስፌት፣ የጥገና አገልግሎት መስጫ ወይም ጋራዥ የሆነ እንደሆነ ሀብቱ ከተያዘ በኋላ ባሉት የተወሰኑ የድርጅቱ የሥራ ቀናትና ሰዓት ደንበኞች ማስረጃቸውን እያቀረቡና ያልተከፈለ የአገልግሎት ቀሪ ሂሳብ እየከፈሉ እንዲረከቡ መደረግ አለበት።

## 14. <u>ልዩ ጥንቃቄ ስለሚያስፈልጋቸው እቃዎች</u>

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12 በተመለከተው መሠረት ሀብት ሲያዝ ልዩ ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸው ልዩ ልዩ ኬሚካሎች ወይም ንጥረ ነገሮች የሚሸጡባቸው፣ የሚከማቹባቸው ወይም የሚመረቱባቸው ሲሆን እነዚህን ኬሚካሎች ወይም ንጥረ



በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2

ነገሮች ለመያዝ የሚያስፈልገው ጥንቃቄ በቅድሚያ መታወቅና አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅት መደረግ ይኖርበታል፡፡

2) ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ሀብት ከመያዙ በፊት ወይም/እና በኋላ ሊበላሽ የሚችልበት ሁኔታ ካለ ሊወሰዱ ስለሚገባቸው እርምጃዎች ዝርዝር ሥርዓት ሊያወጣ ይችላል፡፡

3) ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ በተመለከተው መሰረት ልዩ ጥንቃቄ የሚሹ እቃዎች ስለአያያዙ፣ ስለአጠቃቀሙና አሻሻጡ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ትብብር ሊጠይቅ ይችላል፡፡

## 15. የተያዘ ወይም የተከበረ ሀብት ስለሚለቀቅበት ሁኔታ

1) የተያዘ ወይም የተከበረ ሀብት፡-

ሀ) ለሀብቱ መያዝ ወይም መከበር ምክንያት የሆነው የታክስ ዕዳ በሙሉ የተከፈለ እንደሆነ፣

ለ) ለሀብቱ መያዝ ወይም መከበር ምክንያት የሆነው የታክስ ዕዳ ዋስታና በማስያዝ በስምምነት የታክስ መክፈያ ጊዜው የተራዘመ እንደሆነ፣

ሐ) የታክስ ዕዳው የተሠረዘ ወይም በምህረት እንዲቀር የተደረገ እንደሆነ፣ ወዲያውኑ ይለቀቃል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ1 መሰረት የታክስ ከፋዩ ሀብት የተለቀቀ በሚሆንበት ጊዜ ባለሥልጣኑ በታክስ ባለዕዳው ወጪ ሀብቱን ለሚመዘግብ አካል የመያዝ ወይም የማስከበሩ ትዕዛዝ መነሣቱን መግለጽ አለበት፡፡

## 16. በተያዘ ወይም በተከበረ ሀብት ላይ የሚቀርብ አቤቱታን ስለመመርመር

1) የታክስ ባለዕዳው የተያዘው ወይም የተከበረው ሀብት በሕግ የማይከበር ወይም የማይያዝ ነው በማለት የሀብቱ ሽያጭ ከመካሄዱ በፊት ለባለስልጣኑ አቤቱታ ሲያቀርብለት አቤቱታውን በማጣራት ውሣኔ ይሰጣል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ውሣኔው ሀብቱ መያዝ የለበትም የሚል ከሆነ ሀብቱ እንዲለቀቅ ይደረጋል፡፡

3) የታክስ ባለዕዳው ታክስ ባለመክፈሉ ምክንያት የታክስ ባለሥልጣኑ የያዘው ወይም ያስከበረው ሀብት ይገባናል የሚሉ ሦስተኛ ወገኖች የሚያቀርቡትን አቤቱታ ባለሥልጣኑ ተቀብሎ ይመረምራል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ሀብቱ አላግባብ የተያዘ መሆኑን እና የአቤቱታ አቅራቢው ሀብት መሆኑን በበቂ ማስረጃ ያረጋገጠ እንደሆነ ባለሥልጣኑ የተያዘው ሀብት እንዲለቀቅ ውሣኔ ይሰጣል፡፡



Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
Ministry of ... ARCHIVES 2 ...nance

## 17. ገንዘብ በተያዘ ጊዜ ደረሰኝ ስለመስጠት

1) የታክስ ባለዕዳው በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት ዕዳውን አጠናቆ ባለመክፈሉ በሚሰጥ የመያዝ ትዕዛዝ መሠረት ከታክስ ባለዕዳው እጅ፣ መኖሪያ ቤት ወይም ንግድ ወይም ሥራውን ከሚያከናውንበት ቤት እንዲሁም ከባንክና ከማናቸውም ለታክስ ባለዕዳው ገንዘብ የመክፈል ግዴታ ካለበት ሰው ላይ ገንዘብ የተያዘ እንደሆነ ገቢ ለተደረገው ገንዘብ ደረሰኝ በመስጠት ከታክስ ዕዳው ላይ ሂሣቡ እንዲቀነስ ይደረጋል፡

2) ለዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 አፈጻጸም በአዋጁ አንቀጽ 36 መሰረት ባለስልጣኑ የታክስ ከፋዩን የታክስ እዳ የመክፈል ግዴታ ከተጣለበት ሰው ላይ ገንዘቡን መረከቡን በደብዳቤ ሊገልጽለት የሚገባ ሲሆን ለባለስልጣኑ የከፈለውን ገንዘብ እንዲከፍል ክስ ሊቀርብበት አይችልም ፡፡

3) ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም ባለሥልጣኑ የሚሰጠው ደረሰኝ ለገቨር የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሲሆን ለሻጩ ግን የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ መሂ/1 ነው፡፡

## 18. ሀብትን በመያዝ ለታክስ ዕዳ መክፈያ ማዋልን በውክልና ስለማስፈፀም

1) የታክስ ባለዕዳው ሀብት የሚገኘው ከታክስ ባለሥልጣኑ ዋና መ/ቤት ወይም ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አካባቢ ርቆ በሚገኝ ቦታ እንደሆነ የታክስ ባለዕዳው ሀብት እንዲያዝ የተሰጠውን ውሣኔ ከአስፈላጊ ሠነዶች ጋር በመላክ ሀብቱ በሚገኝበት አካባቢ ባለው የታክስ ባለሥልጣን አማካይነት በውክልና እንዲፈፀም ይደረጋል፡፡

2) ሀብቱ እንዲያዝ የተሰጠው ውሣኔና አስፈላጊ ሠነዶች የደረሰው የገቢ ባለሥልጣን ሀብቱን በመያዝና በመሸጥ ገንዘቡን ለወከለው አካል ማስተላለፍ አለበት፡፡

### ክፍል 3
### የተያዘውን የታክስ ባለዕዳውን ሀብት ስለመሸጥ

## 19. ሀብትን ስለመገመት

1) የታክስ ባለሥልጣኑ ያስከበረው፣ የያዘው ወይም ታሽጐ እንዲቀመጥ ያደረገውን የታክስ ከፋዩን ሀብት ለመሸጥ እንዲችል የሀብት ግምት ሥራ ማከናወን በሚችሉ በሚመለከታቸው አካላት እንዲገመት ያደርጋል፡፡

2) በዚህ ዓይነት የተገመተው የሀብት ዋጋ የግልጽ ጨረታ መነሻ ዋጋ ሆኖ ይወሰዳል፡፡

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
Ministry of Finance ARCHIVES 2

## 20. <u>ሀብት ስለሚሸጥበት ዘዴ</u>

1) የታክስ ባለሥልጣኑ የተያዘውን ወይም የተከበረውን ሀብት ዓይነት፣ ያለበትን ቦታ፣ የሀብቱን ሁኔታ እና ሌሎች ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ሽያጩ በግልጽ ጨረታ ዘዴ የሚከናወን መሆኑን ይወስናል፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በታክስ ባለስልጣኑ የተያዘው ወይም ባለሥልጣኑ የተረከበው ሀብት የሚበላሽ ዕቃ በሚሆንበት ጊዜ የግልጽ ጨረታ ሂደቱን ሳይከተል ሀብቱ የሚሸጥበትን ሌላ ዘዴ ባለስልጣኑ ይወስናል፡፡

3) የታክስ ባለሥልጣኑ በግልጽ ጨረታ የሚሸጠው የታክስ ከፋዩ ሀብት ከአንድ በላይ ከሆነ እንደሁኔታው ሀብቱ በሙሉ በአንድ ጊዜ ወይም ከፊል ሀብቶቹ በቅደም ተከተል እንዲሸጡ ለማድረግ ይችላል፡፡

4) የሀብት ሽያጭ በቅደም ተከተል የሚደረገው የከፊል ሀብቱ ሽያጭ የታክስ ዕዳውን ለመሸፈን የሚበቃ መሆኑ እና ሀብቱን ለመሸጥ ብዙ ጊዜ የማይወስድ መሆኑ ሲታመን ነው፡፡

## 21. <u>የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ ስለማውጣት</u>

1) በታክስ ዕዳ ምክንያት የተያዘው ሀብት በግልጽ ጨረታ  የሚሸጠው የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ ሰፊ ሥርጭት ባለው ጋዜጣ ላይ እንዲወጣ በማድረግ ነው፡፡

2) የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያው የሀብቱን ዓይነት፣ የሀብቱ የግልጽ ጨረታ መነሻ ግምት፣ ሀብቱ የሚገኝበትን ቦታ፣ ግልጽ ጨረታው የሚካሄድበትን ቀንና ሰዓት፣ የሀብቱን ባለቤት ስም፣ በግልጽ ጨረታው ተሳታፊዎች በጨረታው ለመካፈል የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ በተመሰከረለት ቼክ ወይም በሲፒኦ ወይም በጥሬ ገንዘብ እንዲያስይዙ እና የታክስ ባለሥልጣኑ ግልጽ ጨረታውን የመሠረዝ መብት እንዳለው የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

3) የግልጽ ጨረታው ማስታወቂያ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በተደረገው ፎርም ዓይነት መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

4) ማናቸውም የሚንቀሳቀስ ሀብት ሽያጭ በግልጽ ጨረታ የሚከናወነው የግልጽ ጨረታው ማስታወቂያ ጋዜጣ ላይ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ አስራ አምስት ቀን በኋላ መሆን አለበት፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚሸጠው የማይንቀሳቀስ ወይም ልዩ ተንቀሳቃሽ ሀብት የሆነ እንደሆነ ሽያጩ የሚከናወነው የግልጽ ጨረታው ማስታወቂያ ጋዜጣ ላይ ከወጣበት ቀን አንስቶ ከ30 ቀናት በኋላ ይሆናል፡፡

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቤት ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2

6) የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣ በኋላ የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ ያለበትን ገፅ ፎቶ ኮፒ በማድረግ ሕዝብ በሚሰበሰብባቸው ቦታዎች በመለጠፍ በግልጽ ጨረታው የሚካፈሉት ሰዎች ብዛት እንዲጨምር ጥረት መደረግ አለበት፡፡

7) በግልጽ ጨረታ የሚሸጠው ሀብት ከፍተኛ ዋጋ የሚያወጣ ከሆነ በግልጽ ጨረታው የሚሸጠውን ሀብት በሬድዮ ወይም በምስል በማስደገፍ ማስታወቂያው በቴሌቭዥን እንዲተላለፍ ሊደረግ ይችላል፡፡

## 22. ግልጽ ጨረታ ስለማካሄድ

1) የግልጽ ጨረታ ሥነ-ሥርዓቱ ከመጀመሩ በፊት በግልጽ ጨረታ የሚካፈሉ ሰዎች ስም ዝርዝር ይመዘገባል፣ በግልጽ ጨረታው ተሳታፊዎች በጨረታው ለመካፈል ተገቢውን መያዣ በባንክ በተመሰከረለት ቼክ ወይም በሲፒኦ ወይም በጥሬ ገንዘብ እንዲያስይዙ ይደረጋል፡፡

2) በመጀመሪያ ግልጽ ጨረታ በታክስ ዕዳ ምክንያት የተያዘው ሀብት ከግልጽ ጨረታ የመነሻ ዋጋ በታች ሊሸጥ አይችልም፡፡

3) የታክስ ባለዕዳው ወይም የጋራ ባለሀብቶች በጨረታው ለመሳተፍ አስፈላጊውን መስፈርት ካሟሉ እና በግልጽ ጨረታው ላይ ያቀረቡት ዋጋ ከከፍተኛ የግልጽ ጨረታ ዋጋ ጋር እኩል የሆነ እንደሆነ በአንደኛ ደረጃ የታክስ ባለዕዳው በሁለተኛ ደረጃ የጋራ ባለሀብቶች በቅድሚያ የመግዛት መብት ይኖራቸዋል፡፡

4) በባለሥልጣኑ የተያዙ ሀብቶች የሚሸጡበትን ዝርዝር አካሄድ የሚወስንና የጨረታ ስርአቱን የሚወስንና የሚመራ የጨረታ ኮሚቴ ባለስልጣኑ ሊያቋቁም ይችላል ፡፡

## 23. የግልጽ ጨረታ አካሔድ ሥነ-ሥርዓት

በታክስ ባለስልጣኑ የተያዘው ሀብት በግልጽ ጨረታ ሲሸጥ ጨረታው በሚከተለው አኳኋን ይከናወናል፡-

1) የግልጽ ጨረታው ማስታወቂያ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 21(1) መሠረት እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

2) የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ ለመጀመሪያ ጊዜ ከተነገረበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር የ15 ቀን ጊዜ ውስጥ ተወዳዳሪዎች የ ጨረታ ሰነድ ማቅረብ አለባቸው ፡፡

3) የግልጽ ጨረታ ሰነድ ለማቅረቢያ በተወሰነው የመጨረሻ ቀን ሀብቱ የተያዘበት ታክስ ከፋይ ወይም ወኪሉ በተገኘበት ግልጽ ጨረታው ይከፈታል፡፡

4) ለግልጽ ጨረታው ከቀረቡት ተወዳዳሪዎች ከፍተኛ ዋጋ የሰጠው የጨረታው አሸናፊ ይሆናል፡፡

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
የሰነድ ማሟኛ ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation N.. 2
Ministry of
ARCHIVES
2
Finance

5) የግልጽ ጨረታው ውጤት የፀና የሚሆነው የታክስ ባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ ወይም የወከለው ሰው የጨረታውን ሪፖርት ሲያፀድቀው ይሆናል፡፡

## 24. በድጋሚ (ሁለተኛ) ግልጽ ጨረታ ስለማውጣት

1) በታክስ ዕዳ የተያዘው ሀብት በመጀመሪያው ግልጽ ጨረታ ያልተሸጠ እንደሆነ የአንደኛ ግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ በወጣበት አኳኋን ሁለተኛ የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ በማውጣት እንዲሸጥ ይደረጋል፡፡

2) ለድጋሚ የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ አፈፃፀም አግባብ ያላቸው የመጀመሪያ የግልጽ ጨረታ ሥርዓቶች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## 25. በሁለተኛ ግልጽ ጨረታ ስላልተሸጠ ሀብት

1) ሀብቱ በሁለተኛ ግልጽ ጨረታ ያልተሸጠ እንደሆነ የጨረታ ኮሚቴው የመንግሥትን ጥቅም የሚያስጠብቅ መሆኑን ካመነበት የታክስ ባለሥልጣኑ በግምቱ እንዲረከበው ወይም ሦስተኛና ከሦስተኛ በላይ ግልጽ ጨረታ እንዲወጣ ሊያደርግ ይችላል፡፡

2) የታክስ ባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ ወይም የወከለው ሰው ጨረታው በተለየ ሁኔታ እንዲፈፀም ካልወሰነ በስተቀር በሁለተኛው ግልጽ ጨረታ ያልተሸጠው ሀብት በሦስተኛ ወይም ከሦስተኛ ጊዜ በላይ በሚካሄድበት ጊዜ የግልጽ ጨረታውን መነሻ ዋጋ በመቀነስ ሀብቱ እንዲሸጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ሦስተኛ ወይም ከሦስተኛ ጊዜ በላይ የሚደረግ ግልጽ ጨረታ ሲካሄድ አግባብ ያላቸው የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ጊዜ የግልጽ ጨረታ ሥነ-ሥርዓቶች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## 26. የግልጽ ጨረታ አፈጻጸም ሪፖርት ስለማቅረብ

የጨረታ ኮሚቴ፡-

1) ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በሆነው ቅጽ በተመለከተው መሠረት የግልጽ ጨረታውን አካሄድ የሚያሳይ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

2) ሪፖርቱን የግልጽ ጨረታው አስፈፃሚ ከሆነው ኃላፊ አስተያየት ጋር ለታክስ ባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ ወይም ለወከለው ሰው ለውሣኔ ያቀርባል፡

## 27. ሀብት በግልጽ ጨረታ ከተሸጠ በኋላ ስለሚፈፀም ተግባር

1) የተያዘ ሀብት በግልጽ ጨረታ ከተሸጠበት ቀን ጀምሮ በ 15 ቀናት ውስጥ የጨረታው አሸናፊ ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዘውን ገንዘብ እና የውል ማስከበሪያውን 10 % በዕለቱ በልዩ ሂሣብ ለታክስ ባለሥልጣኑ በባንክ ሂሣብ ገቢ ይደረጋል፡፡ ሌሎች ተሳታፊዎች ያስያዙት ገንዘብ ተመላሽ ይሆናል፡፡



Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2

ARCHIVES 2 Finance

2) የግልጽ ጨረታ አሸናፊ ያስያዘውን ገንዘብ ለባለሥልጣኑ በዕለቱ ገቢ ለማድረግ በበቂ ምክንያት ያልተቻለ እንደሆነ በዕለቱ ያልከፈለውን ቀሪ ክፍያ ግልጽ ጨረታው ከተካሄደበት ዕለት ጀምሮ በሚቆጠሩ 15 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ገቢ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

3) አሸናፊው ተጫራች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ገንዘቡን ገቢ ካላደረገ የ7 ቀን ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት በዚህ ጊዜ ውስጥ ካልተከፈለ በጨረታ ወቅት ያስያዘው የውል ማስከበሪያ ገንዘብ ለመንግሥት ገቢ የሚደረግ መሆኑ በፅሑፍ ይገልጽለታል፡፡

4) የግልጽ ጨረታው አሸናፊ ማስጠንቀቂያው ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ7 ቀን ጊዜ ውስጥ በልዩነት የሚፈለግበትን ሂሣብ ገቢ ካላደረገ ግልጽ ጨረታው ተሠርዞ ያስያዘው ገንዘብ ለመንግሥት ገቢ ይደረጋል፡፡

5) የግልጽ ጨረታው አሸናፊ ቀሪውን ሂሣብ ባለመክፈሉ ጨረታው የተሠረዘ እንደሆነ ጨረታው የመጀመሪያ ከሆነ የመጀመሪያ ግልጽ ጨረታ እንዳልተደረገ፣ ሁለተኛ ግልጽ ጨረታ ከሆነ ሁለተኛ ጨረታ እንዳልተደረገ ይቆጠራል፡፡

## 28. <u>የተሸጠውን ሀብት ለገዥው ስለማስረከብ</u>

1) የታክስ ባለሥልጣኑ በግልጽ ጨረታ የተሸጠው ሀብት ዋጋ ሙሉ በሙሉ መከፈሉን ካረጋገጠ ተንቀሳቃሽ ሀብት ከሆነ ለአሸናፊው ወዲያውኑ ያስረክባል፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የሸጠው ሀብት የማይንቀሳቀስ ወይም ልዩ ተንቀሳቃሽ ሀብትና የባለቤትነት ስም ለማዘዋወር ምዝገባ የሚያስፈልገው ከሆነ ባለሥልጣኑ የሀብት ባለቤትነት መብት በገዥው ስም እንዲዘዋወር አግባብ ላለው የመንግሥት አካል በጽሑፍ ያስታውቃል፡፡

3) ባለስልጣኑ በግልጽ ጨረታ የሸጠውን የታክስ ባለእዳ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ሀብት መዝጋቢዎች አካላት ንብረቶች በገዥው ስም እንዲዛወር የሚሰጠውን ትዕዛዝ ባይፈጽሙ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች አግባብ ባለው ህግ መሠረት በህግ ይጠየቃሉ፡፡

## 29. <u>በግልጽ ጨረታ ያልተሸጠን ሀብት ስለማስረከብ</u>

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ 1) እንደተመለከተው ሊሸጥ ያልቻለ ሀብት የታክስ ባለሥልጣኑ እንዲረከበው ውሣኔ የተሰጠ እንደሆነ፣ ይህንኑ ውሣኔ የሀብቱ ባለቤት በፅሑፍ እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡

2) የታክስ ባለሥልጣኑ በግምቱ የተረከበውን ሀብት እስከሚሸጠው ድረስ ለመንግሥት የተሻለ ጥቅም በሚያስገኝ መንገድ ሊያከራይ ይችላል፡፡



በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2

## 30. የታክስ ዕዳን ስለማቀናነስ

1) በግልጽ ጨረታ የተሸጠ ሀብት ወይም ባለሥልጣኑ የተረከበው ሀብት በተሸጠበት ወይም ባለሥልጣኑ በተረከበበት ዋጋ ልክ ታክስ ከፋዩ ከሚፈለግበት ዕዳ እንዲቀነስ በማድረግ የታክስ ክፍያ ደረሰኝ ተቆርጦ ለታክስ ባለዕዳው መስጠት ይኖርበታል፡፡

2) በግልጽ ጨረታ ከተሸጠው ሀብት የተገኘ ገንዘብ በንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከተው መሠረት እንዲቀናነስ ከተደረገ በኋላ ታክስ ከፋዩ ላይ የሚፈለግ ቀሪ ዕዳ ካለ፣ የታክስ ባለሥልጣኑ ለዕዳው ክፍያ የሚውል የታክስ ከፋዩን ሌላ ማናቸውም ሀብት በመያዝ መሸጥ ይችላል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 በተመለከተው መሠረት ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበት ታክስና ሌሎች ወጪዎች ከተቀነሱ በኋላ ተራፊ ገንዘብ ካለው ወዲያውኑ ለታክስ ከፋዩ ይመልስለታል፡፡

## 31. ሀብትን የመያዣና የመሸጫ ወጪዎች

1. የታክስ ባለዕዳውን ሀብት በመያዝና በመሸጥ ለታክስ ዕዳ ክፍያ የማዋል ሥርዓት ወጪዎች የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፡፡

   ሀ) የተሽከርካሪ መጐተቻ ወጪ (towing)
   ለ) የተያዙ ዕቃዎችን ለማጓጓዝ የወጣ ወጪ
   ሐ) የመጋዘን ወጪ ወይም ከሌሎች የታክስ ዕዳ ሀብት ጋር ከሆነ ወጪው ተሰልቶ
   መ) የቁልፍ መቁረጫና አዲስ ቁልፍ መግዣ
   ሠ) የግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ ወጪ
   ረ) ለአጫራቾች የአገልግሎት ክፍያ
   ሰ) ዋጋ ማስገመቻ
   ሸ) የጥበቃ ወጪ
   ቀ) ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ልዩ ልዩ ወጪዎች

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌ

## 32. መሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት በባለስልጣኑ የተያዙ ወይም የተከበሩ ሀብቶች በዚህ መመሪያ መሠረት ፍጻሜ ያገኛሉ፡፡

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
Ministry of Finance ARCHIVES 2

## 33. ሥነስርዓት ስለመዘርጋት

ባለስልጣኑ ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም የሚረዳ የአሰራር ሥርዓት እንደ አስፈላጊነቱ ሊዘረጋ ይችላል፡፡

## 34. የተሻሩ መመሪያዎች

ታክስ የመክፈል ግዴታቸውን ያልተወጡ ታክስ ከፋዮችን ሀብት በመያዝ ወይም በማስከበርና በመሸጥ የታክስ አሰባሰብ የሚከናወንበት ሥርዓት ለመወሰን በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በ9/3/97 በቁጥር አመ3/16 የወጣው መመሪያ በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

## 35. የመመሪያው ተፈጻሚነት

ይህ መመሪያ ከሚያዝያ 1 ቀን 2011 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት 20 ቀን 2011 ዓ.ም**

**አህመድ ሺዴ**
**የገንዘብ ሚኒስትር**

Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2

አባሪ 1

## ገቢዎች ሚኒስቴር

## የታክስ ከፋዩን ሀብት ማስከበሪያ ማስታወቂያ

ቀን ___________

ቁጥር ___________

የተ.እሴት ቁጥር ________

የግብር ከፋዩ መለያ ቁጥር ___________

ለ ___________________________

አድራሻ -አዲስ አበባ --ክፍለ ከተማ ______ ቀበሌ ______________

የቤት ቁጥር ____________የስልክ ቁጥር ___________

ክልል __________ ወረዳ/ከተማ __________ ቀበሌ _______የቤ.ቁ __________

ስልክ ቁጥር ______________

| ተ.ቁ | የታክስ | | የገንዘብ መጠን | | የተከፈለ | | በቀሪ የሚፈለግ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ዓይነት | ዘመን | ብር | ሣ | ብር | ሣ | ብር | ሣ |
| | | | | | | | | |

ከዚህ በላይ መጠኑ የተገለጸውና ለታክስ ባለሥልጣኑ መከፈል ያለበት ታክስ የሚፈለግብዎ መሆኑን በመግለጽ በቁጥር ____________በቀንና በ______________ የተመዘገበው የታክስ ውሣኔ ማስታወቂያ እንዲደርስዎ መደረጉ ይታወቃል።

ሆኖም ተፈላጊውን የታክስ ግዴታዎን ፈጽመው ባለመገኘትዎ ለታክሱ አሰባሰብ በአዋጅ ቁጥር __________ አንቀጽ __________ የታክስ ከፋዩን ማናቸውም ሀብት በመያዝና በመሸጥ /ለታክሱ አሰባሰብ እንዲያውል ለታክስ ባለሥልጣኑ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

ስለሆነም ከዚ በታች የተገለጹትን ____________________________________ ____________________________ሀብቶች ለሚፈለገው ታክስ እና ልዩ ልዩ የአፈጻጸም ወጪዎች ለማዋል በዚህ ማስታወቂያ እንዲከበሩ የተወሰነ መሆኑን እናስታውቃለን።

ከሠላምታ ጋር

የኃላፊ ፊርማ

በኢትዮጵያ የገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ሰነዶች ቁ.2 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2

አባሪ 2

## ገቢዎች ሚኒስቴር

## የሀብት ማስከበሪያ ማስታወቂያ

ቀን ______________

ቁጥር ______________

**ለ /የግብር ከፋዩ ንብረት በእጁ ለሚገኝ ወይም**

**ለግብር ከፋዩ ማናቸውም ዓይነት ክፍያ የመፈጸም ግዴታ ለአለበት/**

-----------------------------------------------------------

የታክስ ባለሥልጣኑ በአዋጅ ቁጥር ____________ አንቀጽ ______________ መሠረት ተወስኖ ለአቶ/ለወ/ሮ ____________________ አድራሻ ____________ክልል _____ ክ/ከተማ ____________ቀበሌ ____________የተ.እሴት ቁጥር ______________ግብር ከፋዩ መለያ ቁጥር ____________በቁጥር ______________ በቀን____________ እንዲደርሰው በተደረገው የታክስ ውሣኔ ማስታወቂያ የተገለጸው ቀጥሎ የተመለከተው፡-

| ተ.ቁ | የግብር/ታክስ | | የግብር/ታክስ መጠን | | የተከፈለ | | ቀሪ ግብር/ታክስ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ዓይነት | ዘመን | ብር | ሣ | ብር | ሣ | ብር | ሣ |
| | | | | | | | | |
| ድምር | | | | | | | | |

በፊደል ______________________________________________

የታክስ ዕዳ ክፍያ ጥያቄ የቀረበ ቢሆንም ግዴታን ለመወጣት ፈቃደኛ ባለመሆን የተጠቀሰው የታክስ ዕዳ ሳይከፈል ይገኛል፡፡

ስለሆነም ይህ ማስታወቂያ ከደረሰዎት ቀን ጀምሮ በታክስ ከፋዩ ስም የተቀመጠ ገንዘብ ወይም ሊከፍሉት የሚገባ ማናቸውም ዓይነት ክፍያ ወይም በእጅዎ/በይዞታዎ/ የሚገኘው የታክስ ከፋዩ ሀብት ወይም በሀብቱ ላይ ያለው መብት በአዋጅ ቁጥር ____________ አንቀጽ ________ መሠረት እንዲከበር የተወሰነ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

የኃላፊ ፊርማ

ግልባጭ፣

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2

አባሪ 3

## ገቢዎች ሚኒስቴር

## ሀብት ስለመያዝ የሚሰጥ ማስታወቂያ

ቀን ____________

ቁጥር ____________

የተ.እሴት ቁጥር ________

የግብር ከፋዩ መለያ ቁጥር ________

ለ ____________________________________

አድራሻ አዲስ አበባ ክፍለ ከተማ ________ ቀበሌ ____________የቤት ቁጥር ________የስልክ ቁጥር ________

ክልል ________ ወረዳ/ከተማ ________ ቀበሌ ----------------የቤ.ቁ ________
ስልክ ቁጥር ____________

| ተ.ቁ | የግብር/ታክስ | | የገንዘብ መጠን | | የተከፈለ | | በቀሪ የሚፈለግ ግብር/ታክስ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ዓይነት | ዘመን | ብር | ሣ | ብር | ሣ | ብር | ሣ |
| | | | | | | | ወለድ | |
| | | | | | | ድምር | | |

ከላይ ለተጠቀሰው የታክስ ዕዳ የታክስ ውሣኔ ማስታወቂያ በቁጥር______በቀን________የተላከ ቢሆንም የታክስ ግዴታ ለመወጣት ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቆይተዋል፡፡

ስለዚህ ይህ ማስታወቂያ ከደረሰዎት ቀን ጀምሮ በ ____________ ቀናት ውስጥ ክፍያ ካልፈጸሙ በአዋጅ ቁጥር ________ አንቀጽ ________ መሠረት ማናቸውም የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ሀብትዎን በመያዝ ለታክስ አሰባሰብ እና ከዚሁ ጋር ለተያያዙ የአፈጻጸም ተግባሮች ማከናወኛ ለሚወጣው ወጪ መሸፈኛ እንዲውል የሚደረግ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

የኃላፊ ፊርማ

ግልባጭ፡

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብት ና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
Ministry of Finance ARCHIVES

# ገቢዎች ሚኒስቴር

## ሀብት ስለመያዝ የሚሰጥ ማስታወቂያ

ቀን ___________

ቁጥር ___________

ለ ______________________________

______________________________

የታክስ ባለሥልጣኑ በአዋጅ ቁጥር __________ አንቀጽ __________ መሠረት ተወስኖ

ለአቶ/ለወ/ሮ ______________ አድራሻ ________ክልል ________ክ/ከተማ ________ቀበሌ ______________የተ.እሴት ቁጥር ____________ግብር ከፋዩ መለያ ቁጥር __________በቁጥር ____________ በቀን__________ እንዲደርሰው በተደረገው የታክስ ውሣኔ ማስታወቂያ የተገለጸው ቀጥሎ የተመለከተው፡

| ተ.ቁ | የግብር/ታክስ | | የግብር/ታክስ መጠን | | የተከፈለ | | በቀሪ የሚፈለግ ግብር/ታክስ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ዓይነት | ዘመን | ብር | ሣ | ብር | ሣ | ብር | ሣ |
| | | | | | | | ወለድ | |
| | | | | | | ድምር | | |

በፊደል ______________________________________________

የታክስ ዕዳ ክፍያ ጥያቄ የቀረበ ቢሆንም ግዴታን ለመወጣት ፈቃደኛ ባለመሆን የተጠቀሰው የታክስ ዕዳ ሳይከፈል ይገኛል፡፡

ስለዚህ ይህ ማስታወቂያ ከደረስዎት ቀን ጀምሮ በአዋጅ ቁጥር ______ አንቀጽ ____ መሠረት በታክስ ከፋዩ ስም የተቀመጠ ገንዘብ ወይም ሊከፍሉት የሚገባ ማናቸውም ዓይነት ክፍያ ለታክስ ባለሥልጣኑ ገቢ እንዲያደርጉ ወይም በእጅዎ/በይዞታዎ የሚገኝ የታክስ ከፋዩ ማናቸውም ሀብት ለታክስ ዕዳ አሰባሰብ እንዲውል ለታክስ ባለሥልጣኑ እንዲያስረክቡ የተወሰነ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

የኃላፊ ፊርማ

ግልባጭ፣

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
Ministry of ... ARCHIVES ... Finance

## ገቢዎች ሚኒስቴር

## የግልጽ ጨረታ ሽያጭ ማስታወቂያ

ታክስ ከፋዩ አቶ/ወ/ሮ ____________________________

የሚፈለግባቸውንታክስብር ________ (________________________) ስላልከፈሉ

አድራሻው __________ከተማ__________ ክፍለ ከተማ ____________ ቀበሌ ______

______ የቤት ቁጥር የሆነውን የታክስ ባለዕዳውን ሀብቶች የኢትዮጵ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በአዋጅ ቁጥር __አንቀጽ__ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በግልጽ ጨረታ ለመሸጥ ይፈልጋል።

1. የሀብቱ የጨረታ መነሻ ዋጋ ግምት ብር ____________ነው።
2. ስለሀብቱ አሻሻጥ መረጃ ከ____ ክፍል ማግኘት ይቻላል።
3. ተጫራቾች በቅድሚያ የጨረታ መነሻ ዋጋ 1/10ኛውን በጥሬ ገንዘብ ወይም ሲ.ፒ.ኦ ማስያዝ አለባቸው።
4. ተጫራቾች ሀብቱን የሚገዙበትን ዋጋ በግልጽ በማስፈር በሰም በታሸገ ኤንቬሎፕ አድርገው አድራሻው በኢትዮጵያ ገቢዎችናጉምሩክ ባለሥልጣን በማለት አስፍረው እስከ _ ቀን ______ ዓ.ም ከቀኑ ______ ሰዓት ድረስ ቢሮ ቁጥር በተዘጋጀው የግልጽ ጨረታ ሳጥን ማስገባት አለባቸው።
5. ጨረታው _______ ቀን ______ ዓ.ም. በቀኑ _____ ሰዓት ተዘግቶ በ _____ ቀን በ_______ ዓመት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በባለሥልጣኑ የስብሰባ አዳራሽ ይከፈታል።
6. አሸናፊው ያስያዘው ገንዘብ ከገዥው ዋጋ ጋር ታስቦ ያሸነፈበትን ጠቅላላ ዋጋ አሸናፊነቱ ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 ቀናት ውስጥ አጠናቆ በመክፈልና ሀብቱን መረከብ አለበት።
7. የጨረታው አሸናፊ ያሸነፈበትን ጠቅላላ ዋጋ በ15 ቀናት ውስጥ አጠናቆ የማይከፍል ከሆን ለጨረታው በዋስትና ያስያዘው ገንዘብ ለመ/ቤቱ ገቢ ሆኖ የጨረታው አሸናፊነቱ ይሠረዛል።
8. ባለሥልጣኑ ስለሀብቶቹ አሻሻጥ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል ሊሠርዝ ይችላል።

Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2
Ministry of ... ARCHIVES 2

አባሪ 6

## ገቢዎች ሚኒስቴር በታክስ ዕዳ ምክንያት የተያዘ ሀብትየግልጽ /ጨረታ ሽያጭ

## አፈጻጸም ሪፖርት

ቀን ____________________

1. ግልጽ /ጨረታው የተካሄደበት ____________ ቀን ____________ ቦታ ______
   ሰዓት ______ ከ ____________ እስከ __________
2. የግልጽ /የጨረታው አስፈጻሚዎች/
   2.1. ________________________
   2.2. ________________________
   2.3. ________________________
   2.4. ________________________
   2.5. ________________________
   2.6. ________________________
3. የታክስ ባለዕዳ ስም ለሚፈለግበት የታክስ ዕዳ አሰባሰብ በ ____________ በወጣው የግልጽ /ጨረታ ማስታወቂያ ዝርዝራቸው ቀጥሎ የተመለከቱት /አባሪ የተደረገው የሀብቶች ዓይነቶች፣ ግምታቸው ብር ____________ ለግልጽ /ጨረታ መነሻ ሆኖ ለሽያጭ የቀረቡ ሲሆን፣
4. በግልጽ /ጨረታ ሽያጭ ለመካፈል የቀረቡ ቅርንጫፎች ዝርዝር ይገለጽ
   4.1. ________________________
   4.2. ________________________
   4.3. ________________________

   መያዣውን በጥሬ ገንዘብ/በቼክ/ስፒኦ/ በማስያዝ ተመዝግበው ተጫርተዋል፡፡
5. የግልጽ /የጨረታው አካሄድ በአጭሩ ይገለጽ፡፡

______________________________________________________________

______________________________________________________ አስተያየት

ቀርቧል፡፡

የግልጽ /ጨረታ አስፈፃሚ ኃላፊ

1. የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ

________________________________

________________________________

ፊርማ ____________

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2
ARCHIVES 2 Finance